# ጅብ ከሚበላህ ይልቅ በልተኸው ተቀደስ!

ጅብ አስቀያሚነቱ ብቻ ሳይሆን ሆዳም፣ የማይራራ፣የማይጠየፍ፣ከርፋታም አውሬ ነው።ጅብ ለሆዱ ሲል የማይሰብረው አጥር የለም፤ጣመውም አልጣመውም ማግበስበስ ይወዳል።እንኳንስ ተርቦ ጠግቦም ቢሆን በቃኝን አያውቅም።እንኳንስ ለሌላው ለራሱም መሰል ጅብ ቢሆን አይመለስም።ለጅብ ዘመዱ ሆዱ ብቻ ነው።በአጭርና እረጂም የኋላና የፊት አራት እግሩ መካከል የተንጠለጠለውን የሆድ አቅማዳ ለመሙላት ያገኘውን ሁሉ ያግበሰብሳል።ጅብ የሚራራለት ፍጡር አይኖርም፤ሁሉም ለእሱ ከርስ ሙሌት የተፈጠረ ይመስለዋል።

እንግዲህ የጅብን ምንነት በጥቂቱም ቢሆን ከተረዳን እንደ ጅብ በቃኝን የማያውቁትን፣የማይራሩና ፣ለሌላው ግድ የማይሰጣቸው የሰው ጅቦች የሆኑትን ሆዳሞች ተግባርና የሚፈጽሙትን ጥቃት መመልከቱ ልዩነታቸውን ወይም መመሳሰላቸውን ለማወቅ ይረዳል።

ከላይ እንደተገለጸው የጅብ ዓላማው ሆዱን ምሙላቱ ነው።በተመሳሳይም የሰው ጅቦችም ዓላማቸው እንደዛው የራሳቸውን ከርስ መሙላት ነው።ከርሳቸውን ለመሙላት ማንኛውንም እርምጃ ከመውሰድ አይቆጠቡም።በአካል የሚመስላቸውን ፍጡር ከማጥቃት አይመለሱም።ጥላቻ፣ስግብግብነት የሚያንቀሳቅሰውን ጭካኔ አንግበው ሊያጠቁ ወደሚፈልጉበት ቦታና ሰው(ሕዝብ)በመንጋና በነጠላ ይዘምታሉ።ጅብ በአብዛኛው  በለሊት ጨለማ ለብሶ የሚንቀሳቀስ ሲሆን ቀኑን ግን በዋሻው ውስጥ ተደብቆ ይውላል።የሰው ጅቦችም በተለያዩ የግልና የመንግሥት ዋሻ በሆኑት ተቋማት ውስጥ ተደብቀው ሥልጣንን ተገን አድርገው የሚያጠቁትን ያጠቃሉ።የጥቃት መፈጸሚያ የተለዩ ሰዓትና ቦታ የላቸውም።ቀኑንም ሌሊቱንም፣ከተማውንም ገጠሩንም በዘረጉት ሰንሰለት ይጠቀሙበታል። ከቶ ማመዛዘን የሚባል ስሜት ስላልተፈጠረባቸው በራሳቸውም ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋ መኖሩን አያስቡም።ከጅብ የሚለያቸው ነገር ቢኖር ባለሁለት እግርና በሰው አምሳያ መፈጠራቸው ብቻ ነው። ሌላው የጅብ መለያ ጸባዩ ለሆዱ መገዛት ነው፤የሚበላውን ከሰጡት ለማዳ ይሆናል።ግን የሱ ለማዳነት የለመደው እስኪቀርበት ድረስ ነው።የለመደውን ሲያጣ አልማጁንም አይምርም።ጅብ የራሱንም መሰል ጅብ ቢሆን አይምረውም፤ከራበው ይዘነጥለዋል።የሰው ጅቦችም እንዲሁ ናቸው፤ላበላቸው ያድራሉ፤ጉርሻው ሲቀርባቸው ደግሞ ያበላቸውን ከደው ሊያጠፉት ይነሳሉ።የውል ሰነዳቸው ጥቅም ነው።ጥቅም ካላገኙ ሰነዳቸውን ይቀዱና ከሌላው ሰነድ ባለቤት ጋር ለመዋዋል ዓይናቸውን አያሹም፤ይሉንታም አያግዳቸውም።በቃላቸው አይረጉም።

ይህንን የጅብ ተልእኮ የሚፈጽሙ በጎሳ ማንነት የሰከሩ ቡድኖችና ስብስቦች በአገራችን መሬት ላይ በቅለው ሕዝብን በማንነቱ በማጥቃትና ከጠላት ለሚወረወርላቸው አንጀ የራሳቸውን አገር ለማፍረስ ከተሰለፉ ዓመታት አልፈዋል፤አሁንም የመጨረሻ የሞት የሽረት ትግል በማድረግ ላይ ናቸው።ከነገ ዛሬ ወደቀልባቸው ይመለሱ ይሆናል በሚልና በሰብአዊነት መነጽር እያዩ በትዕግስት መታለፉን እንደ ፍርሃት የቆጠሩት የሰው ጅቦች ግን ከአድራጎታቸው ሊቆጠቡ አልቻሉም።

በደል የሚፈጸምበትም ምናልባት አምላክ ቢታረቃቸውና ከሰፈረባቸው አዚምና የጅብ መንፈስ ይላቀቁ ይሆናል ብሎ በጾም በጸሎት ቢማጠንም  ግብረ አራዊነታቸው እያደር ጨመረ እንጂ እዩቀነሰ አልመጣም።

ታዲያ ለጅቦቹ ጥቃት የተጋለጠው ሕዝብ ከሚደርስበት አደጋና ጥቃት ለመዳን ምን ማድረግ ይኖርበታል?

በሸጋው የአማርኛ ቋንቋ ተረትና ምሳሌ ወይም ምክረ ቃል ሊበላህ የመጣውን ጅብ በፍርሃት ተውጠህ በዝምታ ከምትጠብቀው ይልቅ አንተም እንደሱ ሆነህ በመጣበት መንገድ መልሰው፣ሌላው ቢቀር በጥርስህም ቢሆን ነክሰህ በማጥቃት ተከላክለህ እራስህን አድን፤ ቢርብህም ጠብሰህ ብላው እንጂ ለጅቡ እራብ ማስታገሻ አትሁን፤ከድል በኋላ የጅብ አካል የነከስከበትንም አፍህን በጠበልና በንስሃ ታጸደዋለህ።የሚል ምክር ይሰጣል።

እዚህ ላይ ተረቱ ወይም ምክሩ ከተራበ ጅብ ጋር የተያያዘ ቢሆንም እንደተራበ ጅብ የሚያደርጋቸውንም የሰው ጅቦች እንዴት አድርጎ መመለስ እንደሚቻልና ሊያደርሱ ከሚችሉት ጥፋትና ጥቃት እንዴት መዳን እንደሚቻል የሚያስተምር መልእክት ይዟል።ያም መልእክት ሊገልህ የመጣውን የጎሳ መንጋ የምትከላከልበትን መሣሪያ ጨብጠህ ጠብቀው፤በለቅሶና በጸሎት ልትመልሰው አትችልም።ሕግና መንግሥት መብትህንና ደህንነትህን የማያስከብር ከሆነ፤ እራስህን በራስህ ለማዳን የምትችለውን ሁሉ አድርግ፤ለራስህ ዘብ ቁም፤ለአገርህ ዘብ ቁም፤ለወገንህ ዘብ ቁም፤በመንጋ የሚዘምቱብህን ህሊና ቢሶች ሃይልህን አስተባብረህ በመመከት ድባቅ ምታቸው።ሁለተኛም እንዳያንሰራሩ አድርገህ ለትውልድ የሚሻገር ታሪክ ሥራ።የሚል ጠንካራ ምክር ያዘለ አባባል ነው።

ለዚህ አልሞት ባይ ተጋዳይ ተገቢ እርምጃ የአቅም ግንባታ ያስፈልጋል።በዬመስኩ መደራጀት ይጠይቃል።የእውቀት፣የገንዘብ ፣የመከላከያ መሳሪያ ትጥቅና ስንቅ መሟላት አለበት። ትልቁ ነገር በራስ መተማመንና የዓላማ ጥራትና ለዓላማው ቁርጠኝነት መኖር ነው።

ለማጥቃት የተሰለፈው ጎሰኛ መንጋ ከቆንጨራና ሜንጫ እስከ ከባድ መሳሪያ የታጠቀ ስለሆነ በተመጣጣኝ ደረጃ መደራጀት ተገቢ ነው።በእርቀት አልሞ ተኩሶ የሚገልን ጠላት በባዶ እጅ ቡጢ አትመክተውም።የግድ ተመሳሳይ ትጥቅ መታጠቅ ያስፈልጋል።

ለዚህ እራስን ለማዳን፣አገርን ለመታደግ ለሚረዳ ተልእኮ ለሰው ልጆች የሚያስቡ፣ለሕግና ፍትህ የሚቆሙ፣ኢሰብአዊነትን፣አውሬነትን፣ጎሰኝነትን የሚቃወሙ ሁሉ ከላይ ለተዘረዘሩት ግብአቶች የሚችሉትን ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።በባዶ ተስፋ የተሞላውና የሚጭበረበረው ወገናቸው ወደ ቀልቡ ተመልሶ ከጥቃት ሊድን የሚችልበትን የሃይል ግንባታ እንዲያደርግ ሊመክሩትና ሊረዱት ይገባል።መምከርም ብቻ ሳይሆን ያልታጠቀውን በሞራልና በመሣሪያ ሊያስታጥቁት ይገባል።በባዶ ቃላት እዬተፈላሰፉ የሞራል ደሃ አያድርጉት።ያለውን እውነታ ሸፋፍነው በማቅረብም አያጭበርብሩት።ሕዝቡን የሹመት መግዣ አያድርጉት።ሕዝቡ በባዶ እጁ የመጣበትን ጠላት ሊቋቋም አይችልም።ጠላትም ሊያከብር የሚችለው ጥንካሬን እያዬ ነውና በሁሉም ዘርፍ መጠንከር የግድ ይላል።ችግር ሲፈጠር ከለቅሶና ከዋይታ ይልቅ ችግሩ ለዘለቄታው የሚወገድበትን መንገድ ማሰብና ለዚያም የሚያስፈልገውን ማድረግ ተገቢ ነው።መጠለያ ላጣው መጠለያና የእለት ጉርሱን ከማቅረብ ባሻገር ለጥቃት ዳግመኛ እንዳይጋለጥ የሚከላከልበት መሳሪያ መሟላት የግድ ይላል።

የትጥቅ ትግል ወደው ወይም ለዝናና ለታይታ የሚሰለፉበት ሳይሆን በጣም አዳጋች፣መራራና ከባድ ውጣ ውረድ የበዛበት፣ለነጻነትና ለሰብአዊ ክብር፣ለዜግነትና ለአገር ህልውና የሕይወት ዋጋ የሚከፍሉበት እንደሆነ አይዘነጋም።ወደው ሳይሆን ተገደው አገርንና እራስን ለማዳን የሚከተሉት መንገድ ነው።የአገር ሕልውናና የሕዝብ መብት በልመናና በመለማመጥ አይከበርም።የአገር ነጻነትና አንድነት የተረጋገጠው በአንድነትና በልዑላዊነት ጥያቄ ላይ በተቃዋሚና ደጋፊ ሃይሎች መካከል በተደረገ የሞት የሽረት ትግል ነው።

ታሪክ እንደሚያረጋግጠውም የአንድነት ሃይሉ በብዛትና በዓላማ ጽናት የበላይ ስለሆነ፣የሚያደርገውም ትግል ፍትሃዊ ስለሆነ የድሉ ባለቤት ይሆናል።

መጀመሪያ ጠላትና ወዳጅን አበጥሮ ማወቅ።የጠላትን ደካማና ጠንካራ ጎን መመርመር።የራስንም ጥንካሬና ደካማ ጎን ፈትሾ ድክመቱን አሶግዶ ጥንካሬውን ማጎልበት ለውጤቱ የመጀመሪያው አመላካች ነው።በዚህ አረገድ በተደጋጋሚ የሚታዬው ድክመት ተበታትኖ በተናጠል በመዳዝ የሚፈልጉትን ሳያገኙ የጥቃት ሰለባ መሆኑን መረዳት ያሻል። ከዚህ ውድቀት ተምሮ እራስን በአንድ ዓላማና ድርጅት ስር ማሰለፍ ተገቢና አስፈላጊ ነው።ዓላማው እራስንና አገርን ከጥፋት ማዳን መሆን አለበት።በጎሳና በጎጥ ወይም በግልና በቡድን ጥቅም ተከፋፍሎ እርስ በርስ እዬተጠላለፉ መሄድ እራስንም አገርንም ለአጥቂዎች ማመቻቸት ነው።አደጋውንም ፈቅዶ መቀበል ነው።

በሌሎቹ ሰላማዊ አገሮች እንኳን ሳይቀር ለምሳሌም በአሜሪካ ሕዝቡ እራሱን ከአደጋ ለመከላከል መሳሪያ የመታጠቅ መብቱ የተከበረ ነው።በአገራችንም እንደዚሁ ዜጋ እራሱን ከአደጋ ለመከላከል የመታጠቅ መብቱ ሊከበርለት ይገባል።የታጠቀው የሚመዘገብና የሚታወቅ ሲሆን በወንጀል ሥራ ላይ የተሰማራ ወይም ሊሰማራ ይችላል ተብሎ የሚጠረጠር፣የአይምሮና የስነምግባር ጉድለት የሚታይበት ሽፍታና አሸባሪ ትጥቅ እንዳይዝ ቁጥጥር ሊደረግበት ይችላል።ለዚህ ብዙ የስነልቦና መመዘኛዎችን ማለፍ ግድ ይላል።

አሁን ወዳለው ብሔራዊ ችግርና አደጋ ስንመለስ አገር አጥፊው ሃይል በተደራጀበት መልኩ ብቻ ሳይሆን ላቅ ባለም መልኩ አገር ወዳዱ ሃይል በፖለቲካው፣በሰው ሃይል፣በገንዘብና ወታደራዊ ተቋም ተደራጅቶ መንቀሳቀሱ የወቅቱ ጥያቄ ነው።ኢትዮጵያ አገራችን አደጋ ውስጥ ስላለች፣የውስጥና የውጭ ጠላቶች የተቀናጀ ዘመቻ ስለከፈቱባት ለኢትዮጵያ ትንሳኤ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ጦር ሃይል ማቋቋም ለነገ የማይሉት ተግባር ነው።ለዚያ በዓላማው የሚስማማ ሁሉ የሚችለውን ማበርከት ይኖርበታል።ከአሁን በኋላ መካሄድ ያለበት ውይይትና ዝግጅት ሃይልን በመገንባቱ ዙሪያ መሆን አለበት።ቀደም ብለው ጥቃቱን ለመከላከል የታጠቁ ቡድኖች ካሉም እነሱን ወደ ሃገራዊ ሕዝባዊ ጦር የሚያድጉበት ሥራ መሠራት አለበት።በአገር ሃብት የተቋቋመው መከላከያ ተብዬው ለተቋቋመበት ዓላማ እንዳልተሰለፈ ብዙ አመላካቾች ታይተዋል።ከአመራሩ ጀምሮ በጎሳ ማንነት ላይ የቆመ ስለሆነ የኢትዮጵያ መከላከያ ብሎ ለመጥራት ያዳግታል።ባለፉትም ተከታታይ የነውጠኞች ጥቃት አብሮነቱን ስላሳዬ እምነት የሚጣልበት አይደለም።በጎሳ አውጫጭኝ የተቋቋመ ስለሆነ የማታ ማታ በጎሳው ጎጆ ውስጥ የመሰግሰጉ ነገር ምስጢር ሊሆን አይችልም።ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ ነው።ከመካከሉ አገራዊ ስሜትና የኢትዮጵያ ፍቅር የሚገዛቸው ቢኖሩ፣መኖራቸውም ስለማይካድ እራሳቸውን ከጎሰኞች አድማና ትዕዛዝ ሊያርቁና ሰልፋቸውን ከአገራዊ ሕዝባዊ ጦሩ ጋር እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

የፖለቲካ ትግል ከመሣሪያው ትግል ተነጥሎ መታዬት የለበትም።ሰላማዊ ትግል የሚሉት ፈሊጥ የሚሰራው ሰላምና ሕግ በተከበረበት አገር ብቻ ነው። አጥቂው በፖለቲካ ድርጅት ብሎም በመንግሥት ደረጃ ድጋፍና ከለላ እስከጥርሱ ታጥቆ በማሸበርና በመግደል በተሰማራበት አገር ተጠቂው ለእልቂት ከመዳረጉ የተለዬ በሰላም መብቱ ተከብሮለት ሊኖር እንደማይችል በተደጋጋሚ ታይቷል።መጃጃሉን አቁሞ ወደ ልቦና መመለስ ጊዜው አሁን ነው።

የትጥቅ ትግሉ አካል የሆነው ሌላው የትግል ዘዴ ደግሞ በኤኮኖሚው ዘርፍ የሚደረገው እምቢ ባይነት ነው።ለአሸባሪ ሃይሎችና ለጎሰኞች ጥቅም ለቆመ መንግሥት ግብአት የሆነውን ምንጭ ማድረቅ ዋነኛው ነው።በዲፕሎማሲም በኩል እንዲሁ የኢትዮጵያ ወዳጅ የሆኑትን ማፍራት ይጠበቃል።

ሕግ ያላስከበረውን መብትና ነጻነት ሃይል ያስከብረዋል!!